የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ-የካቲት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 22
ADDIS ABABA – March 2nd 2007

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፪/፲፱፻፺፱
የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ገጽ ፫ሺ፭፻፹፮

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 132/2007
Ethiopian Police University College Establishment
Council of Ministers Regulations ........... Page 3586

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፪/፲፱፻፺፱ የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፰(፩)መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፪/፲፱፻፺፱ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

፩. "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ መሠረት የተቋቋመ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ቦርድ ነው፤
፪. ‹ሴኔት› ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ መሠረት የተቋቋመ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሴኔት ነው፤
፫. ‹ፕሬዚዳንት› ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ መሠረት የተሾመ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚዳንት ነው፤
፬. ‹ዳይሬክተር› ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫(፪) መሰረት በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሥር የተቋቋመ ተቋም ዳይሬክተር ነው፤
፭. ‹የአካዳሚ ሠራተኛ› ማለት በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ነው፤

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATNS NO. 132/2007 COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN POLICE UNIVERSITY COLLEGE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 8 (1) of the Higher Education Proclamation No. 351/2003.

### PART ONE
### GENERAL

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Ethiopian Police University College Establishment Council of Ministers Regulations No.132/2007"

2. *Definitions*

In these Regulations unless the context requires otherwise:

1) "board" means board of the University College established in accordance with Article 7 of these Regulations;
2) "senate" means senate of the University College established in accordance with Article 12 of these Regulations;
3) "President" means the president of the University College appointed in accordance with article 15 of these Regulations;
4) "Director" means director of an institution established under the University College in accordance with Article 3(2) of these Regulations;
5) "Academic Staff" means any employee of the University College engage in teaching or research activities;

ያንዱ ዋጋ 4:40 [redacted]
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80001

፮. ‹ተጠቃሚ ተቋም› ማለት የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ምሩቃን ቀጣሪ የሆነ ማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም ሲሆን፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ተቋማትን፣ የማረሚያ ቤት አስተዳደሮችን፣ የጉምሩክ ፖሊስንና የህግ አስፈጻሚነትና የህዝብን ጸጥታና ደህንነት የማረጋገጥ ተልዕኮ ያላቸውን ሌሎች ተቋማት ያጠቃልላል።

፫. <u>መቋቋም</u>

፩. የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (ከዚህ በኋላ ‹‹ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ›› ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በሥሩ የሚከተሉትን ተቋማት አካትቶ ይይዛል፤
- ሀ) የፖሊስ እስታፍ ኮሌጅ፤
- ለ) የፖሊስ መደበኛና ልዩ ሥልጠና አካዳሚ ፤
- ሐ) የፖሊስ ጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ኢንስቲትዩት፤
- መ) የወንጀል ምርመራ እና ፎሬንሲክ ሳይንስ ኢንስቲትዩት፤
- ሠ) የፖሊስ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት፤
- ረ) ወደፊት በቦርዱ የሚቋቋሙ ሌሎች ኮሌጆች፣ ኢንስቲትዩቶችና ትምህርት ቤቶች።

፫. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተጠሪነት ለፌዴራል ፖሊስ ይሆናል።

፬. <u>ዓላማ</u>

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

፩. ለህገ መንግስቱ ታማኝ የሆኑና በፖሊሳዊ ሥራ የዳበረ ብቃት ያላቸው የፖሊስ ባለሙያዎችንና መሪዎችን ማፍራት፤

፪. ከፖሊስ ሙያ ጋር የተያያዘ ዕውቀትን ማዳበር፣ ማስፋፋት፣ ማቆየትና ማስተላለፍ፤

፫. የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና አቅምን አፈጻጸም ማጠናከርና ማስፋፋት፤

፬. የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ጥረቶችን ውጤታማነት ማጠናከር፤

፭. የፖሊስ አገልግሎትን የማሻሻልና የማዘመን ሂደት ማፋጠን፤

፮. የህብረተሰቡን ከወንጀልና ከአደጋ ተጋላጭነት ራሱን የመከላከል ሂደት ማገዝ፤

፯. የፖሊስን ተቋም መልካም እይታ በመገንባት ማገዝ።

፭. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሥልጣንና ተግባር</u>

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. በስሩ ፋኩልቲዎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ኢንስቲትዩቶችንና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ክፍሎችን የማቋቋምና የማካሄድ፤

፪. በፖሊስ አገልግሎትና በተያያዥ የጸጥታና ደህንነት መስኮች የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን የመስጠት፤

፫. በተለያዩ የፖሊስ ሥራ መስኮች የልዩ ሙያና የሙያ ማሻሻያ ኮርሶችን የማዘጋጀት የመስጠት፤

፬. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋጽኦ የአካዳሚክ ሜዳል፣ ሽልማትና ማዕረግ የመስጠት፤

፭. የሰልጣኞችን ባህሪ የማጥናት፣ የመገምገም፣ የመቆጣጠር፣ መዝግቦ የማቆየትና ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ፤ የምሩቃንን ሁኔታ የመከታተል፤

6) "stakeholder" means any public body that employs the graduates of the University College, and includes the federal and regional state police departments, penitentiary administrations, customs police and other bodies having responsibilities for law enforcement and maintenance of security and safety;

3. *Establishment*

1) The Police University College (hereinafter the "University College") is hereby established as an autonomous higher education institution having its own legal personality.

2) The University college shall comprise the following institutions:
   (a) the Police Staff College;
   (b) the Basic and Specialized Police Training Academy;
   (C) the Police Medical Professionals Training Institute;
   (d) the Criminal Investigation and Forensic Science Institute;
   (e) the Police Research Institute;
   (f) Other colleges, institutes and schools to be established by the Board.

3) The University college shall be accountable to the Federal Police.

4. *Objectives*

The University College shall have the following objectives:

1) to produce police specialists and leaders who are loyal to the Constitution and professionally qualified;
2) to cultivate, expand, preserve and transmit knowledge pertaining to the profession of police;
3) to strengthen and expand police educational and training capabilities and executions;
4) to enhance the effectiveness of police training endeavors;
5) to speedup the improvement and modernization process of the police service;
6) to assist the public in reducing vulnerability to crimes and accidents;
7) to contribute in the institutional image building of the police.

5. *Powers and Duties of the University College*

The University College shall have the powers and duties to :

1) establish and run colleges, schools, institutes and other academic and research units;
2) design and deliver undergraduate and postgraduate programs in the fields of policing and related public safety and security;
3) design and implement specialized and upgrading training programs in various aspects of policing functions;
4) confer academic certificates, diplomas and degrees as well as medals, prizes and titles for excellence and meritorious contributions;
5) scrutinize, evaluate, regulate and keep records of the behavioral state of trainees and communicate same to the concerned organs, and follow-up the state of graduates;

፮. ለሚሰጣቸው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የመግቢያ፣ የመቀጠያና የመመረቂያ መመዘኛ ዎችን የመወሰን፤

፯. ተልዕኮዎቹን ለመወጣት አስፈላጊ የሚሆኑ የውስጥ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈ ጸም፤

፰. ለፖሊስ አገልግሎት ዋና ዋና የሥራ መደቦች የተፈላጊ ችሎታና ብቃት እስታንዳርዶችን የመለየት፤

፱. የሥልጠና ፍላጎትና ውጤት ትንተናና ግምገማ የማድረግ፤

፲. በፖሊሱ አባላት ዘንድ የመማርና በተማሩት መሰረት የመሥራት ተነሳሽነት ሊስፋፋ የሚችልበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤

፲፩. የፖሊስን ሞያ ለማሳደግ የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን የማድረግና ውጤቱንም የማሰራ ጨት፤

፲፪. ወንጀልን ፣ አደጋንና ግጭትን የሚመለከቱ መረ ጃዎችን የማግኘት፣ የማመንጨት፣ የማደራጀ ትና የማሰራጨት፤

፲፫. ፖሊስ ነክ ህትመቶችንና የማስተማሪያ ጽሑፎችን የማዘጋጀትና የማሰራጨት፤

፲፬. የፌዴራልና የክልል ፖሊስ አመራሮችን የማማ ከር፤

፲፭. ለሌሎች የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት፤

፲፮. በክፍያ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤

፲፯. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸውና ለተልዕኮው መሳካት እገዛ ሊያደርጉ ከሚችሉ የአገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ጋር ግንኙነት የመመሥረት፤

፲፰. ተልዕኮውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሚሆኑ ሰብዓዊ፣ ቁሳዊና ገንዘባዊ ግብዓቶችን የማግኘትና የማስተዳደር፤

፲፱. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ በስሙ የመዋዋል፣ የመክሰስ እና የመከሰስ ፤

፳. ዓላማውን የሚያራምዱ ሌሎች ተግባሮችን የማከና ወን።

፮. ስለተጠቃሚ ተቋማት ተሳትፎ

፩. ተጠቃሚ ተቋማት በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተማሪ ኮታ ድልድል፣ በሚሰጠው ትምህርትና ሥልጠና ይዘት፣ በአዳዲስ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች መከፈትና በነበሩ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች መዘጋት ወይም መታጠፍ ጉዳዮች ላይ ከየራሳቸው የሰለጠነ የሰው ሀይል ፍላጎት አንጻር አስተያየት የማቅረብ መብት ይኖራቸዋል።

፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ቦርድና አመራር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተጠቃሚ ተቋማት አስተያየታቸውን የሚገል ፁበትን መንገድ ማመቻቸትና በጉዳዮች ላይ ሲወስኑም አስተያየቶቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

ክፍል ሁለት

ስለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የፖሊሲና የሥራ አስፈጻሚ አካላት

፯. ስለቦርዱ መቋቋም

፩. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በፌዴራል ፖሊስ ኃላፊ የሚሰ የሙ አንድ ሊቀመንበርና ቁጥራቸው እንደአስፈ ላጊነቱ የሚወሰን አባላት የሚገኙበት ቦርድ ይኖረዋል።

፪. ቦርዱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

፫. የቦርዱ ተጠሪነት ለፌዴራል ፖሊስ ኃላፊ ይሆናል።

6) set entrance, continuation and graduation requirements for the education and training programs it runs;

7) issue and enforce internal rules and standards necessary for the proper execution of its mandates;

8) set competency and qualification standards for major posts in the police service;

9) undertake training needs and impact assessment;

10) promote the interest for learning and application of acquired capabilities among the members of the police;

11) conduct studies and research with a view to upgrading the police profession and disseminate the results thereof;

12) acquire, generate, organize, and disseminate information relating to crime, accident and conflict;

13) produce and distribute police related publications and teaching materials;

14) consult federal and regional state police leaders;

15) provide technical assistance for other federal and regional state police training institutions;

16) provide paid consultancy services;

17) establish relations with other local and foreign institutions having similar objectives and potentials to assist in accomplishing its mission;

18) acquire and administer the human, material and financial resources that are necessary for the fulfillment of its objectives;

19) own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

20) carry out such other activities as are necessary for the attainment of its objectives.

6. *Involvement of Stakeholders*

1/ Stakeholders of the University college shall have the right to comment, in view of their trained manpower requirements, on students' quota assignments, the contents of educational and training programs, opening of new programs and closure or merger of existing programs.

2/ The Board and management of the University College shall facilitate the involvement of stakeholders and consider their comments in making decisions on issues referred to in sub-Article (1) of this Article.

*PART TWO*

*POLICY AND EXECUTIVE BODIES OF THE UNIVERSITY COLLEGE*

7. *Establishment of the Board*

1) The University College shall have a Board that consists of a chairperson and members to be designated by the chief of the Federal Police.

2) The Board shall have its own Secretary.

3) The Board shall be accountable to the Chief of the Federal Police.

፰. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. ይህ ደንብ እንደአስፈላጊነቱ እንዲሻሻል ለመንግሥት ሃሳብ ያቀርባል፤

፪. ከመንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር በተገናዘበ መልኩ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና እና የአስተዳደር ፖሊሲ ያወጣል፣ ያስፈፅማል፤

፫. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አደረጃጀት ይወስናል፤

፬. የተጠቃሚ ተቋማት ተሳትፎን የሚያስችሉ ተገቢ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን ያረጋግጣል፤

፭. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶችን ለመንግሥት አቅርቦ ያሾማል፤ የዳይሬክተሮችን ሹመት ያጸድቃል፤

፮. የተባባሪ ፕሮፌሰርና የፕሮፌሰር ማዕረግ ያፀድቃል፤

፯. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዓመታዊ እቅድና የበጀት ጥያቄ ይመረምራል ፣ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፰. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥር፣ ዕድገት፣ ዲሲፕሊን፣ አበልና ጥቅማ ጥቅም የሚወስን የውስጥ አስተዳደር ደንብ አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ያስፈጽማል፤

፱. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች መንግሥት ባፀደቀው መመሪያ መሠረት ይወስናል፤

፲. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች ያጸድቃል፤

፲፩. ማንኛውም የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ ደረጃውን ጠብቆ የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን መለያ ምልክት ወይም ዓርማ ይወስናል፤

፲፫. የራሱን የስብሰባና የአሰራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል ፤

፲፬. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

፱. ስለፖሊስ ሥልጠና መማክርት መቋቋም

፩. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ይዘት፣ አወቃቀርና ሂደት ወጥ የሆነ ስታንዳርድ ያላቸውና አገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮችን በሚገባ አጣጥመው የሚያስኬዱ እንዲሆኑ ከማስቻል አንጻር የፖሊስ ሥልጠና መማክርት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪. መማክርቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ) የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚዳንት ......... ሰብሳቢ

ለ) የምርምር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ...... አባል

ሐ) የሌሎች የፌዴራልና ክልል ፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋማት መሪዎች ...... አባላት

መ) በቦርዱ የሚሰየሙ ሌሎች አካላት .... አባላት

፫. የመማክርት ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል።

፬. መማክርቱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

፭. መማክርቱ ቢያንስ በአንድ በጀት ዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል።

8. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the powers and duties to:

1) propose, where necessary, amendments to these Regulations for Government approval;
2) issue the general academic and administrative policy of the University College in conformity with Government policies and laws, and ensure the implementation of same;
3) determine the organizational structure of the University College;
4) ensure that appropriate mechanisms are established to facilitate the participation of stakeholders;
5) submit nominations of appointments for posts of the President and Vice President for approval of the Government; approve the appointments of directors;
6) approve conferring of the ranks of associate professors and professors;
7) determine the plan and draft budget of the University college and monitor the implementation of same upon approval;
8) prepare internal administrative rules that determine conditions of employment, promotion, discipline, allowances and benefits of the academic staff of the University College, and applies after confirmation by the Government;
9) determine fees to be charged by the University College in accordance with directives approved by the Government;
10) approve agreements made by the University College with third parties;
11) decide on appeals against decisions made by any organ of the University college, when submitted to it in compliance with the line of hierarchy;
12/ approve the emblem of the University College;
13/ determine its own rules of procedure;
14/ perform such other activities as may be necessary for the attainment of the objectives of the University College.

9. *Establishment of the Police Training Assembly*

1) There is hereby established the Police Training Assembly, with the aim to maintain national standards and to ensure proper consideration of both national and local issues in all police training programs.
2) The Assembly shall have the following members:
   (a) the President of the University College .... ................................. Chairperson
   (b) the Director of the Police Research Institute....................Member
   (c) Heads of other federal and regional police training institutions ....... Members
   (d) other persons to be designated by the Board ............................ Members
3) The Assembly shall be accountable to the Board
4) The Assembly shall have its own secretary.
5) The Assembly shall meet at least twice in a budget year.

፲. <u>የፖሊስ ሥልጠና መማክርት ዓላማና ተግባሮች/</u>

ቦርዱ የሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ መማክርቱ የሚከተሉት ዓላማና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. ወጥነትንና ተቀራራቢነትን የሚያረጋግጡ አገር አቀፍ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት በሁሉም የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ዘንድ ተፈጻሚ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፪. በሁሉም የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት መካከል በአገር አቀፍ ደረጃ ጥሩ ቅንጅትና ህብረት እንዲኖር ያደርጋል፤

፫. በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጁ የፖሊስ ሥልጠና እቅዶች ላይ በመወያየት ማሻሻያ አስተያየት ይለዋወጣል፤

፬. አገር አቀፍ የፖሊስ ሥልጠና ሂደቶችን ይገመግማል፣ ተሞክሮ ይለዋወጣል፤

፭. በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፲፩. <u>የሴኔት መቋቋም</u>

፩. የሚከተሉትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሴኔት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

ሀ) የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚዳንት........ ሰብሳቢ

ለ) የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ............. አባላት

ሐ) ዳይሬክተሮች ........................... አባላት

መ) የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሬጅስትራር ............. አባል

ሠ) የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ ................. አባል

ረ) የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መምህራን ጉዳይ ኃላፊ .............. አባል

ሰ) ከየትምህርትና የሥልጠና ተቋማቱ የተወከሉ አንዳንድ መምህራን......አባላት

ሸ) የተማሪዎች ካውንስል ሁለት ተወካዮች ..........አባላት

ቀ) የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሴቶች ጉዳይ ተወካይ ...... አባል

በ) በቦርዱ የሚሰየሙ ሌሎች ሰዎች ........አባላት

፪. ሴኔቱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

፫. የሴኔቱ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል።

፲፪. <u>የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ሴኔቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የፕሮግራሞችና ኮርሶች መከፈትን፣ መሻሻልንና መዘጋትን ያጸድቃል፤

፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የትምህርት ካሌንደር መርምሮ ያፀድቃል፤

፫. ከዳይሬክተርና ሙሉ ፕሮፌሰር በታች ያሉ የአካዳሚክ ሠራተኞች ምደባዎችንና ማዕረጎችን ያጸድቃል፤

፬. የዳይሬክተሮችንና ፕሮፌሰሮችን ሹመትና ማዕረግ መርምሮ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፭. ቦርዱ ያወጣቸውን ፖሊሲዎች መሠረት በማድረግ የአካዳሚክ መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ያፀድቃል፤

10. *Objectives and Duties of the Police Training Assembly*

Subject to the general directives issued by the Board, the Assembly shall have the objectives and duties to:

1) formulate national standards for police training and ensure the observance of such standards by all police training institutions;
2) ensure the establishment of proper networking and collaboration among all police training institutions in the country;
3) discuss and exchange views on police training plans prepared at national level;
4) evaluate national level police training practices with a view to sharing experiences;
5) perform other duties pursuant to the directives of the Board.

11. *Establishment of the Senate*

1) There is hereby established the Senate of the University College having the following members:
   (a) President of the University College ....................... Chairperson
   (b) Vice Presidents of the University College .................. Members
   (c) Directors ............................... Members
   (d) Registrar of the University College .................. Member
   (e) Head of the Student Affairs Office ............ Member
   (f) Head of the Academic Staff Affair Office ............. Member
   (g) a representative of the academic staff from each education and training institution ............................ Members
   (h) two students' council representatives ................... Members
   (i) Head of the University College's Women Affairs Office ....... Member
   (j) other persons designated by the Board ................................... Members
2) The Senate shall have its own secretary.
3) The Senate shall be accountable to the Board.

12. *Powers and Duties of the Senate*

Subject to the general directives issued by the Board, the Senate shall have the powers and duties to:

1) approve the opening, revision and closure of programs and courses;
2) examine and approve the academic calendar of the University College;
3) approve academic appointments and promotions below the rank of director and professor;
4) recommend to the Board academic appointment and promotions to the ranks of directors and professors;
5) approve academic rules and standards in line with the policy set by the Board;

፮. ዲግሪዎች፣ ዲፕሎማዎች፣የምስክር ወረቀቶች፣ ሜዳይና ሌሎች የአካዳሚክ ሽልማቶች እንዲሰጡ ይወስናል፤
፯. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፲፫. የፕሬዚዳንቱና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሹመትና ተጠሪነት

፩. ፕሬዚዳንቱ በቦርዱና በፌዴራል ፖሊስ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል፣ ተጠሪነቱም ለቦርዱ ይሆናል።
፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚዳንቶች በቦርዱ አቅራቢነት በፌዴራል ፖሊስ ይሾማሉ፤ ተጠሪነታቸውም ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል።

፲፬. የፕሬዚዳንቱ ሥልጣንና ተግባር

ፕሬዚዳንቱ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መሪና ዋና አስፈፃሚ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአካዳሚክና አስተዳደራዊ ሥራዎች በዋና ኃላፊነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
፪. የፖሊስ ሥልጠና መማክርትን ይሰበስባል፤ የውሳኔዎቹንም ተፈጻሚነት ይከታተላል፤
፫. በቦርዱና በሴኔቱ የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈጻሚ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
፬. የተጠቃሚ ተቋማትን ፍላጎቶች ለማካተት የሚያስችሉ ሥርዓቶች መበጀታቸውን ያረጋግጣል፤
፭. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ስትራቴጂክና ዓመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ፤ ሲጸድቁም ተፈጻሚነታቸውን ያረጋግጣል፤
፮. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አጠቃላይ ተቋማዊ የሥራ አፈጻጸም ደረጃ ይከታተላል፣ ያሻሽላል፤
፯. አግባብነት ያላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
፰. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን በመወከል ስምምነቶችንና ውሎችን ይፈርማል፤
፱. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ይወክላል፤
፲. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ስም የባንክ ሒሳብ እንዲከፈትና እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤
፲፩. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የየሩብ ዓመትና ዓመታዊ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ዘገባዎች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤
፲፪. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲፭. የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. በአካዳሚክ ጉዳዮች ፕሬዚደንቱን ያግዛል ፣ ያማክራል፤
፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአካዳሚክ ሥራዎች ይመራል፣ ያስተባብራል፤
፫. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚሰጡ ትምህርትና ሥልጠናዎች ሕገመንግሥታዊ ግንዛቤን፣ ፖሊሳዊ ስብዕናን እና ሙያዊ ብቃት ከመገንባት አንጻር ደረጃቸውን የጠበቁ መሆና ቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

6) decide on conferring of degrees, diplomas, certificates, medals and other academic awards;
7) perform such other activities as may be assigned to it by the Board.

13. *Appointments and Accountability of the President and Vice-Presidents*

1) The President shall be appointed by the Government upon the recommendation of the Board and the Federal Police, and shall be accountable to the Board.
2) The Vice Presidents of the University College shall be appointed by the Federal Police upon recommendation of the Board and shall be accountable to the President.

14. *Powers and Duties of the President*

The President shall be the Chief Executive of the University College and shall have the powers and duties to:

1) direct and control the academic and administrative activities of the University College as a head;
2) chair the Police Training Assembly and follow up the implementation of its decisions;
3) ensure the implementation of decisions passed by the Board and the Senate;
4) ensure that appropriate mechanisms are established to incorporate the interests of the stakeholders;
5) prepare and submit plans to the Board strategic and annual work plans and budgets of the University College, and ensure their implementation upon approval;
6) monitor and improve the overall institutional performances of the University College;
7) ensure the observance of the relevant laws, regulations and directives;
8) sign agreements and contracts on behalf of the University College;
9) represent the University College in all its dealings with third parties ;
10) open and operate bank accounts in the name of the University College;
11) prepare and submit to the Board quarterly, annual and other necessary periodic reports on the activities of the University College;
12) perform other activities as may be assigned to him by the Board.

15. *Powers and Duties of the Academic Vice president*

The Academic Vice president shall have the powers and duties to:

1) support and advise the President on academic matters;
2) direct and co-ordinate the academic affairs of the University College;
3) follow up the teaching and training courses offered by the University College and ensure that they meet all relevant standards concerning constitutional understanding, police personality and competencies;

፬. በሚሰጡ ፕሮግራሞች አዘገጃጀት፣ ይዘትና አሰጣጥ ተሳታፊዎቹ የሚሰማሩባቸው ሥራዎች ልዩ ሁኔታና የተጠቃሚ ተቋማት ፍላጎት የተጤነበት መሆኑን ያረጋግጣል፤
፭. የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ዝግጅትን፣ የፕሮግሞች አፈጻጸም ሂደት አመራርንና የጥናትና ምክር አገልግሎት ሥራዎች አፈጻ ጸምን የሚመለከቱ ስታንዳርዶችና ሥርዓቶች መዘጋጀታቸውንና መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
፮. የፖሊስ ጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲስፋፉና የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች የፖሊሱን አገልግሎት ለማሻሻል እንዲበቁ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፯. አካዳሚክ ካውንስሉን ይሰበስባል፤ የሴኔቱ፣ የአመራር ኮሚቴውና የአካዳሚክ ካውንስሉ ውሳኔዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
፰. የዳይሬክተሮችን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤ የሌሎች የአካዳሚክ ሠራተኞችን የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ሁኔታን ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤
፱. የአካዳሚክ ዘርፉን ዓመታዊ እቅድና የበጀት ፍላጎት ያዘጋጃል፤
፲. የአጫጭር ኮርሶችን፣ ወርክሾፖችን፣ ሴሚናሮ ችንና ኮንፈረንሶችን ዝግጅትና አፈጻጸም ይከታ ተላል፤
፲፩. የጥናትና ምርምር፣ የካሪክለም ቀረጻና ማሻሻያ እንዲሁም የማስተማሪያ ጽሁፍ ዝግጅት ሥራዎችን ይከታተላል፤
፲፪. የአካዳሚክ ዘርፉን ሪፖርት እንደየአስፈላጊነቱ እያዘጋጀ ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤
፲፫. የአካዳሚክ ሠራተኞችን የቅጥርና የውል ዕደሳ ጥያቄዎችን ተቀብሎ በመመርመር ለአመራር ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
፲፬. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ወክሎ የአካዳሚክ ሠራተ ኞችን የቅጥር ውል ይፈራረማል፤
፲፭. ፕሬዚዳንቱ በሌለበት ተክቶት ዩኒቨርሲቲ ኮሌ ጁን ይመራል፤
፲፮. በፕሬዚዳንቱና በሴኔቱ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

፲፮. <u>የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. በአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ፕሬዚዳንቱን ያግዛል፣ ያማክራል፤
፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአስተዳደርና ልማት ሥራዎች ይመራል፣ ያስተባብራል፤
፫. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኞችና ተማሪዎች ዘንድ ስለህገ መንግስቱ፣ ስለአገራዊ ፖሊሲ ዎችና የትኩረት ጉዳዮች፣ ስለፖሊስ ደንቦችና መመሪያዎች፣ ስለተፈላጊ የፖሊስ ስብዕናዎችና ባህሪያት ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባሮችን ያስፈጽማል፤
፬. የድጋፍ ሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገትና የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ይቆጣጠራል፤
፭. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአስተደደርና ልማት ዘርፍ ሪፖርት እንደየአስፈላጊነቱ እያዘጋጀ ለፕሬዚዳ ንቱ ያቀርባል፤

4) ensure that the specific job requirements to be assumed by the participants and the interests of the stakeholders are considered in the designing, content and presentation of all programs offered;
5) ensure that the necessary standards and procedures are formulated and maintained for designing teaching and training courses, managing programs and for processing research and consultancy service activities;
6) create enabling environment for the enhancement of police research activities and for the utilization of the research outcomes in improving the police service delivery;
7) chair the Academic Council; ensure that the decisions of the Senate, the Management Committee and the Academic Council are implemented;
8) manage the performances of the directors; facilitate and oversee the performance management process of other academic staff;
9) prepare the annual plan and budget proposal of the academic branch;
10) follow up the preparation and execution of short courses, workshops, seminars and conferences;
11) follow up the process of research undertakings, designing and improvement of curricula and preparation of teaching materials;
12) submit periodic reports on academic affairs to the President as may be required;
13) examine requests for employment of academic staff and renewal of their contracts and forward his recommendations to the Management Committee;
14) sign employment contracts of the academic staff on behalf of the University College;
15) act on behalf of the President in the absence of the later;
16) perform such other duties as may be assigned to him by the president and the Senate.

*16. Powers and Duties of the Vice President for Administration and Development*

The Vice President for Administration and Development shall have the powers and duties to:

1. support and advise the President on the administrative and development activities of the University College;
2. direct and co-ordinate the administrative and development activities of the University College;
3. carry out activities that may help students and staff of the University College to develop their understandings of the Constitution, national policies and priorities, police regulations and directives and the requisite police personality and traits;
4. supervise the employment, promotion, and performance management of the administrative personnel;
5. submit periodic reports on administrative and developmental affairs of the University College to the president as may be required;

፮. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሰው ኃይል ፍላጎት መሟላቱንና የሠራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣ ዕድገት፣ ስንብትና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች አግባብ ባላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤ ሠራተኞች መብታቸው ተከብሮላቸው ግዴታቸውን እንዲወጡ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፤

፯. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ንብረት አግባብ ባላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ያስተዳድራል፤ ለመማር ማስተማር ሂደት የማያስፈልጉ ቁሳዊ አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

፰. ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎችና ማህበረሰብ የሚያስፈልጉ የጤና፣ የምግብና መኝታ፣ የትራንስፖርት፣ የጥበቃና የመሳሰሉ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መመሪያ የተወሰኑ አገልግሎቶችና አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

፱. ከመንግሥት መደበኛ በጀት በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የፋይናንስ አቅም ለማጠናከር የሚያስችሉ የገቢ ምንጮችን ያስፋፋል፣ ገቢውን በአግባቡ ያስተዳድራል፤

፲. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአስተዳደርና ልማት ዘርፍ አመታዊ በጀትና ዕቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተፈጻሚ ያደርጋል፤

፲፩. በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲፯. የምርምር ተቋም ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

የጥናትና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የጥናትና ምርምር እና አየምክር አገልግሎት ሥራዎች የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱን ያግዛል፣ ያማክራል፤

፪. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የጥናትና የምርምር እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፫. የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲስፋፉና የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች የፖሊሱን አገልግሎት ለማሻሻል እንዲበቁ ያደርጋል፤

፬. የጥናትና ምርምር ፍላጎቶችን ይለያል፤ የጥናት ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፤ የጥናት ፕሮጀክት ወጪ መሸፈኛ አማራጮችን ይፈልጋል፤ የጸደቁ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን አፈጻጸምና ውጤት ይከታተላል፤

፭. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤

፮. የሥልጠና ፍላጎትና ውጤት ግምገማ በየወቅቱ መደረጉንና የሚያስፈልጉ የፕሮግራም ማስተካከያዎች መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፯. የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ህትመትና ሥርጭት ያመቻቻል፤

፰. በጥናትና ምርምር ጉዳዮች ላይ ሥልጠናዎችን፣ ወርክሾፖችን፣ ሴሚናሮችንና ሲምፖዚየሞችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፤

፱. በሌሎች የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ተቋማት የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ጥረቶችን ያግዛል፣ ያበረታታል፤

6. ensure that the manning requirements of the University College are met, and that the recruitment, transfer, promotion and dismissal of staff and other personnel matters are effected in accordance with the relevant laws, regulations and directives; take the necessary measures to ensure that employees are able to enjoy their rights and to discharge their responsibilities;
7. manage the University College's property in accordance with the appropriate laws, regulations and directives; ensure the availability of materials required for the teaching-learning activities;
8. ensure the satisfactory provision of health, food and accommodation, transport, security and such other services and supplies the students of the University College and other members of its community are entitled to in accordance with directives of the University College;
9. expand income-generating schemes to strengthen the financial position of the University College, apart from the normal budgetary allocation by the Government, and properly administer the proceeds thereof;
10. prepare annual budgets and plans for the University College's administrative and development activities, and implement same upon approval;
11. perform such other activities as may be assigned to him by the president.

*17. Powers and Duties of the Director of Research Institution*

The Director of research institution shall be accountable to the Academic Vice President and shall have the powers and duties to:

1. Support and advise the Academic Vice President on the research and consultancy activities of the University College;
2. direct and co-ordinate the research and consultancy services of the University College;
3. ensure the enhancement of research activities and the utilization of the research outcomes in improving the police service delivery;
4. identify research priorities; prepare research project proposals; identify alternative funding sources for research projects; monitor the execution and outcome of research projects upon approval;
5. prepare the long and medium term strategies of the University College;
6. ensure that training need and impact assessments are conducted regularly and necessary program adjustments are effected;
7. facilitate the publication and distribution of research results;
8. prepare and conduct trainings, workshops seminars and symposiums on research issues;
9. assist and promote research activities carried out by other federal and regional state police institutions;

፲. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎች ለመመረቂያ ማሟያ የሚያደርጉዋቸውን ጥናቶች ሂደት ያስተባብራል፤
፲፩. ለጥናትና ምርምሩ ተቋም አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችና ሥርዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
፲፪. መምህራንና ተማሪዎች በጥናትና ምርምሩ ሥራ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤
፲፫. የጥናትና ምርምሩን ተቋም ዓመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ያስፈጽማል፤
፲፬. የተቋሙን ሠራተኞችና የአጥኚዎችን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤
፲፭. ለጥናትና ምርምሩ ሥራ አስፈላጊ የሚሆኑ የአሰራርና አፈጻጸም መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ተፈጻሚነታቸውን ያረጋግጣል፤
፲፮. የተቋሙን የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ሪፖርቶች እያዘጋጀ ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤
፲፯. በጥናትና ምርምር ጉዳዮች ላይ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲፰. የትምህርትና የሥልጠና ተቋም ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

የማንኛውም የትምህርትና የሥልጠና ተቋም ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የተቋሙን አካዳሚክና አስተዳደራዊ ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
፪. የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ፣ የወርክ ሾፖችና የሲምፖዚየሞች ዝግጅትና አፈጻጸም ሂደቶችን ይመራል፤
፫. የተቋሙን አካዳሚክ ኮሚሽን ይሰበስባል፤
፬. ለተቋሙ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችና ሥርዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
፭. በተቋሙ ውስጥ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በሙሉ ተገቢ ስታንዳርዶችን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
፮. የህገ መንግስታዊ መርሆዎች ማስረጽና የፖሊሳዊ ስብዕና ግንባታ ስትራቴጂዎች ተፈጻሚ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
፯. የተቋሙን የአካዳሚክና የድጋፍ ሠራተኞች አፈጻጸም ይገመግማል፤
፰. ለተቋሙ ሠራተኞችና ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መመሪያ መሰረት ሊቀርቡ የሚገቡ አቅርቦቶችና አገልግሎቶች ተሟልተው መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
፱. የተቋሙን ዓመታዊ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅም ያስፈጽማል፤
፲. የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች አፈጻጸም ንና የሰልጣኞችን ሁኔታ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
፲፩. በትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ላይ አስፈላጊ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ አስተያየት ያቀርባል፤
፲፪. የተቋሙን የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ሪፖርቶች እያዘጋጀ ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤
፲፫. በትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች ላይ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

10. direct the process of studies conducted by students of the University College as partial fulfillment of degree programs;
11. secure resources and establish systems required for the research institution;
12. encourage the teaching staff and students to engage in research;
13. prepare the annual plan and budget of the research institution, and implement same upon approval;
14. manage the performances of researchers and other staff of the institution;
15. formulate and ensure the observance of guidelines and procedures applicable to research activities;
16. prepare and submit to the Academic Vice President periodic reports on the activities of the Institution;
17. perform other duties pertaining to research activities as may be assigned to him by the Academic Vice President;

*18. Powers and Duties of Director of Education and Training Institution*

The Director of education and training institution shall be accountable to the Academic Vice President and shall have the powers and duties to:

1. direct and administer the academic and administrative activities of the institution;
2. manage the process of designing and delivering educational and training programs, workshops and symposiums;
3. chair the academic commission of the institution;
4. secure resources and establish systems required for the institution;
5. ensure that all training programs offered by the institution meet the required standards;
6. ensure the implementation of strategies design-ed for propagating constitutional principles and nurturing of police personality;
7. manage the performances of the academic and support staff of the institution;
8. ensure the proper provision of facilities and services to staff and students of the institution as prescribed in the directives of the University College;
9. prepare annual plans and budgets of the institution and implement same upon approval;
10. monitor and evaluation the execution of educational and training programs and the situation of students;
11. propose necessary improvements on educational and training programs;
12. prepare and submit to the Academic Vice President periodic reports on the activities of the institution;
13. perform other duties pertaining to education and training as may be assigned to him by the Academic Vice President;

፲፱. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሌሎች አካላት

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሌሎች የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ክፍሎች አመሰራረትና አሰራር እንዲሁም የአመራር አካላቱ አሰያየም በቦርዱ ይወሰናል።

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳. በጀት

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፤

፩. በመንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤
፪. ከሚሰበሰባቸው የአገልግሎት ክፍያዎች፤ እና
፫. ከሌሎች ምንጮች።

፳፩. የሂሳብ መዛግብት

፩. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
፪. የኮሌጁ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፳፪. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፳፫. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

*19. Other Organs of the University College*

The establishment and functions of other education, training and research components of the University College and the designation of their organs shall be determined by the Board.

## *PART THREE*
## *MISCELLANEOUS PROVISIONS*

*20. Budget*

The budget of the University College shall be drawn from:

1. budgetary appropriations by the Government;
2. collection of fees; and
3. other source.

*21. Books of Accounts*

1. the University College shall keep complete and accurate books of accounts.
2. the books of accounts and financial documents of the University College shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

*22. Inapplicable Laws*

No regulations or directives, in so far as they are inconsistent with the provisions of these Regulations, shall be applicable to matters provided for in these Regulations.

*23. Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

*Done at Addis Ababa, this 27th day of April, 2007.*

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE